# የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

## የደረጃ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴና
## የስራ ግብረ-ሃይል አባላት ማትጊያ ክፍያ
## መመሪያ

586/2013

ጥር 2006 ዓ.ም

ኢደኤ/ESA
11 ኛው የምክር ቤት ስብሰባ
የሰነድ ቁጥር ዓ/ገ003/10

# የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

## የደረጃ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴ የስራ ግብረ-ሃይል አባላት

## ማትጊያ ክፍያ መመሪያ

### መግቢያ

በአገሪቱ ለሚገኙ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪነትና ለአገር እድገት የደረጃ ዝግጅት ስራ ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ፤

ደረጃዎች የሚዘጋጁት ከተለያዩ ተቋማት በተወጣጡ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት መሆኑንና የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ይህንን ሂደት በሴክሬታሪያትነት የሚመራና የሚያስተባብር መሆኑን በመገንዘብ፤

በዚህ የደረጃ ዝግጅት ሂደት የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ሙያዊ አስተዋፅኦ ወሳኝነት፣ ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪነት የሚሰሩት መሆኑንና ከእውቀት ክክሎትና ልምድ በተጨማሪ ትኩረትና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

በአንፃሩ ባለሙያዎች ከየመጡበት ተቋም ለዚህ ሥራ ክፍያ የሚፈጸምበት አሰራርና ዝግጁነት ገና ያልተፈጠረ በመሆኑ፣ ይህን ክፍተት ለመሙላት መንግሥት የማትጊያ ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስፈልገው በመረዳትና ቀደም ብሎ ይሰራበት የነበረው መመሪያ አሁን ካለው ወቅታዊ ሁኔታ እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 193/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 እና በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ይህን የማትጊያ መመሪያ አውጥቷል።

### 1. አጭር ርዕስ፡-

ይህ መመሪያ "የደረጃ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴና ግብረ ሃይል አባላት ማትጊያ ክፍያ" የብሔራዊ የደረጃዎች ምክር ቤት መመሪያ 586/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ትርጓሜ፡-

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1 "ቴክኒክ ኮሚቴ" ማለት ለኢትዮጵያ ደረጃ ዝግጅት ስራ የተደራጀና የመንግስት እውቅና ያለው አካል ነው።

2.2 "የስራ ግብረ ኃይል" ማለት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቴክኒክ ኮሚቴ በስሩ አደራጅቶ የሚያሰራው የባለሙያዎች ስብስብ የያዘ የደረጃ ዝግጅት የስራ ቡድን ነው፡፡

2.3 "ማትጊያ ክፍያ ማለት" ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የሚከፈል አበል ሆኖ ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላትና ለስራ ቡድን አባላት በቁጥር የሚከፈል ክፍያ ወይም በውል መሠረት የሚፈፀም ክፍያ ነው፡፡

## 2. አላማዎች፡-

ይህ መመሪያ የሚከተለው አላማ ይኖረዋል፡፡

3.1 የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት፣ በስራ ግብረ-ሃይል የሚመደቡ ባለሙያዎች፣ የደረጃ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴ ፀሐፊዎችና ፕሮጀክት ማኔጀሮች ተነሳሽነትና ፈቃደኝነት እንዲጨምር እንዲሁም በደረጃ ዝግጅት ስራ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ባለሙያዎች ቁጥር እንዲጨምር ማድረግና ስራው በከፍተኛ ትኩረት ጥንቃቄና ጥራት ባለው መልኩ እንዲሰራ ለማድረግ የሚያግዝ የማትጊያ ክፍያ ስርዓት ለመትከል ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን፡-

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው በኤጀንሲው ስር ተደራጅተው ሕጋዊ እውቅና ላላቸው ብሔራዊ የደረጃ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴዎችና እነርሱ ለሚያቋቁሟቸው የስራ ግብረ-ሃይሎች አባላት ሲሆን የገንዘብ ክፍያንና በስብሰባ ጊዜያት የሚደረግላቸውን የሻይ/ቡና ውሃና ምሳ መስተንግዶን ያካተተ ይሆናል፡፡

## 4. የማትጊያ ክፍያ አፈፃፀም፡-

የማትጊያ ክፍያ ለአባላት የሚፈፀመው የቴክኒክ ኮሚቴዎች ወይም የስራ ግብረ-ሃይሎች የየፕሮጀክቶቻቸውን ስራዎች አጠናቅቀው ማስረከባቸው በደረጃ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት ሲረጋገጥ ሆኖ የክፍያ ሁኔታና አፈፃፀም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

5.1 የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በፕሮጀክት ብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ ለእያንዳንዳቸው ይከፈላል፣ለሊቀመንበሩ ብር 1100.00/አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር/ይከፈላል፡፡

5.2 የቴክኒክ ኮሚቴና የስራ ግብረ-ሃይል ስብሰባ በሚካሄድበት እለት

በስብሰባ ላይ ለተገኙ አባላት ብር 200/ ሁለት መቶ ብር /ለእያንዳንዳቸው ይከፈላል፡፡ ሊቀመንበሩ ወይም ተወካይ ስለ ፕሮጀክት አፈፃፀም ለማስረዳት በብሔራዊ የደረጃዎች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ሲገኝ ብር 200/ሁለት መቶ ብር /ይከፈላል፡፡

5.3 ለስራ ግብረ-ሃይል አባላት በፕሮጀክት ብር 2000/ሁለት ሺህ ብር/ ለእያንዳንዳቸው በጥቅሉ የሚከፈል ሆኖ በተጨማሪ በፕሮጀክቱ ስር ለተዘጋጁ ደረጃዎች በተጨማሪ በአንድ ደረጃ ብር 200/ ሁለት መቶ ብር/ለእያንዳንዳቸው ይከፈላል፡፡

5.4 ለቴክኒክ ኮሚቴ ፀሐፊዎች የፕሮጀክት ስራ ተጠናቅቆ ደረጃዎቹ ሲፀድቁ በዬሩብ ዓመት ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡ የስራ ግብረ-ሃይል አባል ሆኖ(ና) ለተመደበ(ች) ፀሐፊ ለሌሎች የግብረሃይሉ አባላት የሚከፈለው መጠን ይከፈለዋል(ላታል)፣ ሆኖም ከአንድ ፕሮጀክት በላይ አይከፈልም፡፡

5.5 በጥናትና ምርምር ላይ ተመስርተው ለሚዘጋጁ ደረጃዎች የተቋቋመ የስራ ግብረ-ሃይል ከኤጀንሲው ጋር በሚደረግ ልዩ የውል ስምምነት መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 5. የተሻሩ ሕጎች፡-

ይህ መመሪያ ፀድቆ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በቀድሞ የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን የደረጃዎችና ሰርተፊኬት ካውንስል ፀድቆ ሲሰራበት የቆየው (ደሠካሰ05/04) መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 6. የመመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፡-

ይህ መመሪያ በብሔራዊ የደረጃዎች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከጥር 07/2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ኢ.ደ.ኤ/ESA

11 ኛው የምክር ቤት ስብሰባ

የሰነድ ቁጥር ዓካ 003/10